በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሠ/መ/ቁጥር 216482
ሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም

**ዳኞች ፦ብርሃኑ አመነዉ**

**ተሾመ ሽፈራዉ**

**ሀብታሙ እርቅይሁን**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**ነጻነት ተገኝ**

**አመልካች፡- አቶ ግርማ ጋዲሳ፡- ቀረቡ**

**ተጠሪዎች፡-1. አቶ መገርሳ ጋዲሳ**

**2. ወ/ሮ ወርቄ አበራ** } **ቀረቡ**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጋራ በስጦታ ተገኘ የተባለ ንብረት አጠቃቀም የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሰዉን በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ክልል ውስጥ የሚገኘው 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ከተጠሪዎች ጋር በ2003 ዓ/ም አቶ ጣሰው አበራ የተባለ ግለሰብ በስጦታ ለአመልካችና ለ1ኛ ተጠሪ ሰጥተዉናል፡፡በቦታዉም ላይ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ቤት ሰርተንበት ይዞታችን አድርገን በቤቱም እስካሁን እየኖርንበት እንገኛለን፡፡ ሆኖም ግን ቦታውን እኩል መካፈል ስገባን ተጠሪዎች ግን ቦታውን በስማቸው የግል ይዞታቸዉ አድርገው እንዳስመዘገቡ ተረድቻለሁ፡፡በመሆኑም ስጦታ አድራጊው እኩል እንድንካፈል የሰጠንን 300 ካሬ ሜትር ቦታ ያለአግባብ በድብቅና በሕገ-ወጥ መንገድ በተጠሪዎች ስም የተመዘገበው እንዲሰረዝ ፣ ይዞታው በአመልካች እና በተጠሪዎች ስም በጋራ እንዲመዘገብና እኩል 150 ካሬ ሜትር በየግላችን ተካፍሎ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ አቶ ጣሰዉ በ2003 ዓ/ም ለአመልካችና ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ ስላላስተላለፉ በክሱ ላይ የተገለጸዉ ፍሬ ነገር ሀሰት ነዉ፡፡አመልካች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/1 ፣2428 እና 2443 መሰረት በጽሁፍና በምስክሮች ፊት የተደረገ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የስጦታ ዉል በማስረጃነት ያላቀረቡ ስለሆነ ስጦታ ተደርጎልኛል በማለት ያቀረቡት ክስ የሕግ መሰረት የሌለዉ ነዉ፡፡ ክርክር የተነሳበት ይዞታ አቶ ጣሰው አበራ በቀን 20/02/1992 ዓ/ም ለተጠሪዎች በስጦታ ያስተላለፉት ነው፡፡ ተጠሪዎች በቦታው ላይ ምንም አይነት ተቃውሞ ሳይኖር አሁን ያሉትን ግንባታዎች በራሳችን ገንዘብና ጉልበት ሰርተናል፡፡በመሆኑም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1179/1 እና በሰ/መ/ቁጥር 36638 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሰረት የተጠሪዎች የግል ንብረት ነዉ፡፡ አመልካች የተጠሪዎች ጥገኛ ሆነዉ ተጠሪዎች በሰራነው ቤት ውስጥ ከመኖር ባለፈ በቤቱ ላይ ምንም መብት ስለሌላቸዉ ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 129931 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና የአቶ ጣሰው አበራንና የወ/ሮ አረጋሽ ጫላን ምስክርነት ቃል ሰምቶና መዝኖ በቀን 09/02/2014 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ክርክር የተነሳበትን ይዞታ አቶ ጣሰዉ አበራ በ2003ዓ/ም ለአመልካችና ለተጠሪዎች በስጦታ እንዳስተላለፉ የመሰከሩ ቢሆንም አመልካች ቦታዉን በስጦታ ያገኙ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 እና 2443 መሰረት ሥልጣን ባለዉ አካል ፊት የተደረገ ወይም በግልጽ ኑዛዜ አደራረግ ሥርዓት መሰረት የተደረገ የሰነድ ማስረጃ በማስረጃነት በማቅረብ አላስረዱም፡፡ይዞታዉን በስጦታ ሰጡ የተባሉት ግለሰብ በሰጡት ምስክርነት በይዞታዉ ላይ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በይዞታዉ ላይ ቤት ሰርተዉ የሚኖሩ መሆኑን ቢመሰክሩም ለተጠሪዎች ይዞታዉን ሙሉ በሙሉ ለማስተላለፍ ያልፈረሙ መሆኑን በሰጡት ምስክርነት ቃል አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች የስጦታ ውሉን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን መጠየቅ አይችሉም እንጂ በይዞታዉ ላይ መብት ያላቸዉ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ተገንዝቧል፡፡ ነገር ግን አመልካች ይዞታዉን በስጦታ ያገኙ ስለመሆኑ ያላስረዱ በመሆኑ በስጦታ ዉሉ መሰረት ክስ ለማቅረብ አይችሉም በማለት ፍርድ ከሰጠ በኋላ ፍርዱ አመልካች ቤት ሰርተዉ እየኖሩበት ባለዉ ቤት እና ይዞታ ላይ መብት የላቸዉም የሚያሰኝ ዉጤት የለዉም ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ 279931 ላይ በቀን 22/02/2014 ዓ/ም በተሰጠ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞባቸዋል፡፡ አመልካች በቀን 13/03/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡-የስጦታ ውል ስለመደረጉ ባልተካደበትና የስጦታ ዉሉ ፎርምን አልተከተለም በሚል ምክንያት አመልካች ክስ ለመመስረት መብት የላቸዉም መባሉ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡ የአጻጻፍ ስርዓት ያልተከተለ ዉል በሕጉ በተመለከቱት ሰዎች እንዲፈርስ እስካልጠየቁ ድረስ በሰ/መ/ቁጥር 53328 ላይ እንደተወሰነዉ ከጅምሩ ፈራሽ ነዉ የሚባል አይደለም፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ስጦታ የተደረገዉ በሌላ ሶስተኛ ወገን በመሆኑ ተጠሪዎች ስጦታ ተቀባዮች እንጂ ስጦታ በአድራጊዎች ካለመሆናቸዉም በተጨማሪ ሥጦታ አድራጊዉ ግለሰብ ቀርበዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ በስጦታ መስጠታቸዉን መስክረዉ እያለ የስር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1ን እና 2443ን ጠቅሶ ዉሉ ፎርማሊቲዉን አላሟላም ሲል የሰጠዉ ውሳኔ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡በተከራካሪ ወገን የዉል ፎርማሊቲን የሚመለከት ክርክር ቀርቦ ዉሉ እንዲፈርስ እስካልቀረበ ድረስ ፍርድ ቤቱ በራሱ

አነሳሽነት የአጻጻፍ ሥነ ሥርዓትን መሰረት በማድረግ ዉድቅ ሊያደርግ አይችልም፡፡የስር ፍርድ ቤት በዚህ መልኩ የሰጠዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 43825 ላይ የተሰጠዉን ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤት በአንድ በኩል የስጦታ ዉሉ ሰነድ እስካልቀረበ ዉሉ ከመሰረቱ የሕግ ዉጤት ስለሌለዉ አመልካች የመጠየቅ መብት የላቸዉም እያለ በሌላ በኩል አመልካች የሥጦታ ዉሉን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን መጤቅ አይችሉም እንጂ በይዞታዉ ላይ መብት እንዳላቸዉ አረጋግጫለሁ በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ስለዉሎች መፍረስና ሕጋዊ ዉጤት በሕግ የተደነገገዉን የተከተለ አይደለም፡፡ስጦታ አድረጊዎች ዉል በ2000ዓ/ም ፈርመናል እያሉ የስር ፍርድ ቤት ይህንን ዉል ሳያስቀርብ የሰጠዉ ዉሳኔ ፍርድ ቤቶች ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ተጨማሪ ማስረጃ ማስቀረብ አለባቸዉ በሚል በሰ/መ/ቁጥር 22603 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ከአመልካች ጋር በጋራ በመያዝ ስንጠቀም የቆየነዉን ይዞታ ተጠሪዎች ለብቻቸዉ ማስመዝገባቸዉ ተገቢ አይደለም ተብሎ በጋራ የያዝነዉን ይዞታ እኩል 150 ካሬ ሜትር እንዲንካፈል ይወሰንልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነው ይዞታ ለአመልካችና ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ የሰጡ ስለመሆኑ ባለይዞታዉ የነበሩት አቶ ጣሰው አበራ ስር ፍርድ ቤት በመቅረብ ባስረዱበት ሁኔታ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በቀን 26/04/2014 ዓ/ም የተፃፈ መልሳቸውንን ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- ለክርክር መነሻ የሆነውን ይዞታ አመልካች በስጦታ ተላልፎልናል ይበሉ እንጂ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881፣2427፣2428 እና 2447 መሰረት ቢያንስ በ4 ምስክሮች ፊት የተፈረመና በጽሁፍ የተቋቋመ የስጦታ ዉል በማስረጃነት በማቅረብ የማስረዳት ሸክም እያለባቸው የስጦታ ውል በማስረጃነት አያይዘው አላቀረቡም፡፡ በሕጉ አግባብ የተቋቋመ የስጦታ ውል ባልቀረበበት ሁኔታ አቶ ጣሰው አበራ አመልካችን ለመጥቀም ሲሉ ስጦታ ሰጥቻለው የሚል ምስክርነት ቢሰጡም ይህ ምስክርነት በሀሰት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ እንደ በቂ ማስረጃ ሊቆጠር አይችልም፡፡አንድ ሰዉ ስጦታ ሰጥቻለሁ ስላለ ብቻ በሕጉ አግባብ የተቋቋመ ውል ሳይኖር ውል አለ የሚል የህሊና ግምት ማሳደር አይቻልም፡፡ እንዲሁም የግለሰቡ ምስክርነት በሰነድ ማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ ስህተት ስለሌለ የቀረበው አቤቱታዉ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በቀን 13/05/2014 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ጭብጥ ከግምት በማስገባት በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች በክሱ ላይ እንደገለጹት በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረቱት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን 300 ካሬ ሜትር ይዞታ አቶ ጣሰዉ አባራ ለእኔና ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ ሰጥተዉን በየራሳችን ቤት

ሰርተንበት በቤቱ እየኖርን እየተገለገልንበት እያለ ተጠሪዎች ከሕግ አግባብ ዉጭ በድብቅ የይዞታዉን ስመ ሀብት በስማቸዉ እንዳስመዘገቡ ስለተረዳሁ በስማቸዉ የተመዘገበዉ ተሰርዞ ይዞታዉን ለሁለት እኩል እንዲንካፈል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት በመጠየቅ ነዉ፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ አመልካች ይዞታዉን አገኘሁኝ ያሉበትን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881 እና 2443 መሰረት የሕጉን ፎርማሊቲ አሟልቶ የተደረገ የስጦታ ዉል በማስረጃነት ካለማቅረባቸዉም በተጨማሪ ይዞታዉን አቶ ጣሰዉ አበራ ለተጠሪዎች ብቻ በስጦታ ሰጥተዉን ቤት ሰርተን ይዘን የምንገኝበት ስለሆነና አመልካች ከተጠሪዎች ጋር በጥገኝነት ከመኖር ባለፈ ባለይዞታ ስላልሆኑ ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አቶ ጣሰዉ አበራንና የወ/ሮ አረጋሽ ጫላን ምስክርነት ሰምቶ እነዚህ ምስክሮችም ይዞታዉ የአቶ ጣሰዉ የነበረ መሆኑን፣በዚህ ይዞታ ላይ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ወንድማማቾች ስለሆኑ በይዞታዉ ላይ የየራሳቸዉን ቤት ሰርተዉ እየኖሩ እንሚገኙና ለተጠሪዎች ይዞታዉን በስጦታ ለማስተላላፍ እንዳልፈረሙ ከሰጡት ምስክርነት ቃል ማረጋገጡን ገልጾ አመልካች ቤት ሰርተዉበት በሚኖሩበት ቤትና ይዞታ ላይ መብት የላቸዉም ባይባልም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 እና 2443 መሰረት የተደረገ የሥጦታ ዉል በማስረጃነት ያላቀረቡ በመሆኑ የስጦታ ዉል መሰረት በማድረግ ክስ መመስረት አይችሉም ሲል መወሰኑን የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡

ከዚህ በላይ በተመለከተዉ መሰረት ከተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር መረዳት የሚቻለዉ አመልካች በይዞታዉ ላይ የባለይዞታነት መብት አገኘሁበት የሚሉት የስጦታ ዉል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 እና 881 መሰረት የተደረገ ስለመሆኑ የሚያሳይ ሰነድ በማስረጃነት አቅርበዉ ማስረዳት እንዳልቻሉ ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማጣራትና የመመዘን ሥልጣን ባላቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡የአመልካች የክስ ይዘት እንደሚያሳየዉ አመልካች በክሳቸዉ ላይ ስለስጦታ ዉል የጠቀሱት የይዞታዉ ባለይዞታ የሆኑበትን መንገድ ለማሳየት እንጂ በቀጥታ የስጦታ ዉል ይፈጸምልኝ ለማለትና ክርክሩን የዉል ክርክር ለማድረግ አይደለም፡፡በክሱ የጠየቁትም ዳኝነት በስጦታ ዉሉ መሰረት ይፈጸምልኝ የሚል ሳይሆን በጋራ ይዘን ቤት ሰርተን የምንገለገልበትን ይዞታ እኩል እንዲንካፈል ይወሰንልኝ የሚል መሆኑ የሚያሳየዉም የክሱ መሰረት የባለይዞታነት መብት ለማስከበርና በይዞታዉ ላይ የተሰራዉን ቤት ከመፋለም ጋር የተያያዘ ስለሆነ የንብረት ክርክርን የሚመለከት እንጂ የዉል ክርክርን የሚመለከት አለመሆኑን ነዉ፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ እንደተመለከተዉ ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ የከሳሽን መብት ለመመስረት የሚያስችል እና/ወይም ለተከሳሹ መከላከያ ለመሆን የሚችል በክስ አቤቱታ፣ በመከላከያ መልስ፣ በማስረጃ ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 241 መሰረት ተከራካሪዎች ተመርምረዉ በሰጡት መልስ ላይ እና በሕግ ላይ ተመስርቶ የሚያዝ ነዉ፡፡ በያዝነዉ ጉዳይ ከላይ እንደተመለከተዉ የአመልካች ክስ መሰረት የንብረት ባለመብትነትን መፋለምን የሚመለከት ነዉ፡፡እንዲሁም ተጠሪዎች የስጦታ ዉሉን ፎርማሊቲ የሚመለከት ክርክር ስላቀረቡ በዚህ ችሎት አመልካች በሰበር አቤቱታቸዉ ላይ የሰ/መ/ቁጥር 43825 ጠቅሰዉ የፎርማሊቲ ክርክር ተጠሪዎች ሳያነሱ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ማንሳቱ ተገቢ አይደለም በሚል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ሆኖም ተጠሪዎች የስጦታ ዉሉ አድራጊዎች አለመሆናቸዉ ፣ ክሱ ላይ ከላይ እንደተመለከተዉ ስለስጦታ ዉል የተገለጸዉ ይዞታዉ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የተገኘበትን መንገድ ለማሳየት ብቻ መሆኑና ክርክሩ ንብረትን መፋለምን የሚመለከት ክርክር መሆኑ ከግምት ገብቶ ሲታይ አመልካች ይዞታዉን አገኘሁበት ያሉት የሥጦታ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 እና 881 ስር የተደነገገዉን የዉል አመሰራርት ፎርማሊቲን የሚያሟላ ነዉ ወይስ አይደለም የሚል ጭብጥ በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ ጭብጥ አይደለም፡፡

የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ እንደሚያሳየዉ የስር ፍርድ ቤት ምስክሮችን ሰምቶ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ የአቶ ጣሰዉ አበራ እንደነበርና በአከራካሪዉ ይዞታ ላይ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የየራሳቸዉን ቤት ሰርተዉ የመሬት ይዞታዉን ይዘዉ እየተጠቀሙ እንደሚገኙ በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጧል፡፡በአንድ ሰዉ የመሬት ይዞታ ላይ ባለይዞታዉ ሳይቃወም ሕንጻ የገነባ ሰዉ የህንጻዉ ባለቤት እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1179/1 ስር ተደንግጓል፡፡ከዚህ የሕግ ድንጋጌ አተገባበር ጋር በተያያዘ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 30101 ላይ (በቅጽ 6 እንደታተመዉ) እና በሰ/መ/ቁጥር 96628 ላይ(በቅጽ 17 እንደታተመዉ) አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች እየተከራከሩ ያሉት በአከራካሪዉ ይዞታ ላይ ቤት መስራት የቻሉት ይዞታዉን ባለይዞታዉ አቶ ጣሰዉ አበራ ቤት እንዲሰሩበት ለእሳቸዉና ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ ሰጥተዋቸዉ እንደሆነ በመግለጽ ነዉ፡፡ በእርግጥ አንድን ይዞታ ባለይዞታዉ ቤት ሰርቶ እንዲገለገልበት ለሌላ ሰዉ በመፍቀድ የሚፈጽመዉ ድርጊት እና ይዞታዉን በስጦታ ዉል መስጠት እንደነገሩ ሁኔታ በንብረት ሕግና በዉል ሕግ መሰረት ታይቶ ሕጋዊ ዉጤታቸዉ ሊወሰን የሚገባ ነዉ፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ የአመልካች ክስ መሰረቱ እና ዳኝነት ጥያቄያቸዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ ባለመብትነትንና ባለይዞታዉ ላይ የተሰራ ቤት ባለሀብትነት መብትን በመፋለም ይዞታዉን መከፋልን የሚመለከት እስከሆነ ድረስ በጭብጥነት ተይዘዉ ከማስረጃና ከሕግ አንጻር ተረጋግጠዉ ሊወሰኑ የሚገባቸዉ ጭብጦች፡-ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ አመልካች ቤት በሰሩበት ጊዜ የማን የነበረ ነዉ? አመልካች አከራካሪዉን ይዞታ የያዙትና በይዞታዉ ላይ ቤት የሰሩት ባለይዞታዉ ፈቅደዉላቸዉ ነዉ ወይ? በአከራካሪዉ ይዞታ ላይ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የየራሳቸዉን ቤት ሰርተዉ እየኖሩ ከሆነ የየራሳቸዉን ቤት መስራት የቻሉት ባለይዞታዉ ይዞታዉን ለአመልካች እና ለ1ኛ ተጠሪ በጋራ ሰጥተዉ ወይም ፈቅደዉላቸዉ ነዉ ወይስ አይደለም? ወይም ባለይዞታዉ አከራካሪዉን ይዞታ ቤት ሰርቶ እንዲገለገልበት የፈቀዱት ወይም በስጦታ የሰጡት ለማነዉ? የሚሉ ናቸዉ፡፡ ሆኖም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን እነዚህን ጭብጦች በመያዝ በግራ ቀኙ በተቆጠሩ ማስረጃዎች እና ፍርድ ቤቱ አስቀርቦ የሰማቸዉ ምስክሮች ከሰጡት ምስክርነት ቃል አንጻር መርምሮና መዝኖ በሚያረጋግጠዉ ፍሬ ነገር ላይ ተመስርቶ በአመልካች ዳኝነት ጥያቄ ላይ ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ ጉዳዩን ከሥጦታ ዉል ፎርማሊቲ አንጻር ብቻ በማየት አመልካች የሕጉን ፎርማሊቲ በጠበቀ መልኩ የተደረገ የስጦታ ዉል ሰነድ በማስረጃነት ስላላቀረቡ በተጠሪዎች ላይ ክስ ለማቅረብ አይችሉም በማለት የምስክሮች ቃል እና ሌሎች ማስረጃዎችን ሳይመረምርና ሳይመዝን የሰጠዉ ዉሳኔ የክርክር አመራርና የማስረጃ ምዘና መርሆዎች አተገባበር ጉድለት ያለበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

# ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 129931 ላይ በቀን 09/02/2014 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 279931 ላይ በቀን 22/02/2014ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት በአብላጫ ድምፅ ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ ከላይ በፍርዱ ክፍል የመጨረሻ ፓራግራፍ ላይ የተጠቀሱትን እና ተያያዥ ጭብጦችን በመያዝ በማስረጃ አጣርቶና ማስረጃዎችን መዝኖ ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

# ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስከለ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

## የልዩነት ሃሳብ

እኔ ስሜ በሁለተኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰዉ ዳኛ በአብላጫዉ ድምጽ ዉሳኔ ስላማልስማማ የልዩነት ሃሳቤን እንደሚከተለዉ አስፍረያለሁ፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ አቶ ጣሰዉ አበራ በ2003 ዓ.ም ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ሰጥቶአቸዉ ተረክበዉ ቤት ሰርተዉ ሲኖሩበት እንደነበረ እና በኋላ ይዞታዉን ለሁለት እንካፈል በሚል ስጠይቀዉ 1ኛ ተጠሪ ፍቃደኛ ካለመሆኑም በላይ ይዞታዉን በግሉ አስመዝግቧል የሚል ሲሆን፣ የጠየቀዉ ዳኝነትም ይዞታዉ ለሁለት እኩል እንዲካፈል ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ በሰጡት መልስ አቶ ጣሰዉ ይዞታዉን ለተጠሪዎች እንጂ ለአመልካች አልሰጠም እንዲሁም ቤቱን ያለምንም ተቃዉሞ በራሳቸዉ ገንዘብና ጉልበት የሰሩ መሆኑንና በአመልካች ገንዘብ የተሰራ ቤት አለመኖሩን ጠቅሶ ተከራክረዋል፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ዓላማ እና ግብ የፍትሐብሔር ጉዳዮች በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ ፍትሐዊ ዉሳኔ እንዲያገኙ ማድረግ ሲሆን፣ ይህን ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድም ህጉ የተለያዩ መርሆዎችን እና ደንቦችን ይደነግጋል፡፡ በህጉ የተመለከቱትን ደንቦች እና መርሆዎች በክርክር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ ክርክሩ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብትን ባረጋገጠ መልኩ የሂደቱ ፍትሐዊነት እዉን በማድረግ በመጨረሻ ላይ የሚሰጥ ዉሳኔም ፍትሐዊ እንዲሆን የሚስያችል ስለመሆኑ እሙን ነዉ፡፡ በህጉ በተለያዩ ድንጋጌዎች ዕዉቅና ከተሰጣቸዉ ደንቦች እና መርሆዎች ዉስጥ አንዱ የጭብጥ አያያዝ ሥርዓትን የሚመለከት ነዉ፡፡ በዚህም የህጉ አንቀጽ 246(1) ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችላቸዉን ትክክለኛ ጭብጥ መያዝ እንዳለባቸዉ የሚያስገነዝብ ሲሆን፤ ጭብጥ የሚያዘዉም ግራ በጽሁፍ ያቀረቡትን ክስ እና መልስ፣ በህጉ አንቀጽ 241 መሠረት ክስ ሲሰማ ግራ ቀኝ ያነሱትን ክርክር እንዲሁም ማስረጃን መሠረት በማድረግ እንደሆነም በአንቀጽ 248 ላይ ከተመለከተዉ ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች ይዞታዉ በጋራ የተሰጠን ነዉ በማለት ዳኝነት የጠየቀ ቢሆንም ተጠሪዎች ስጦታዉ በጋራ አልተሰጠንም የሚል ክርክር ያቀረቡ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ እልባት ለመስጠት መያዝ የሚገባዉ ትክክለኛ ጭብጥ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ይዞታ ለአመልካች እና ለተጠሪዎች በጋራ የተሰጠ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚል ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(3) ላይ እንደተመለከተዉ የገጠርም ሆነ የከተማ ይዞታ መብት የሚገኘዉ በመንግስት ወይም፣ በህግ አግባብ በሚደረግ የስጦታ ዉል፣ ከግለሰቦች በሚሰጥ ስጦታ ወይም በዉርስ ሲሆን ከእነዚህ ዉጪ በዘፈቀደ የይዞታ ባለመብት መሆን አይቻልም፡፡ በአብላጫዉ ድምጽ ዉሳኔ እንደተመለከተዉ አመልካች ያቀረበዉ ክስ መፋለምን የሚመለከት ሲሆን፣ በክሱ የይዞታ መብቱ ምንጭ ስጦታ መሆኑን የጠቀሰዉም በዚሁ መነሻነት እንደሆነ ይታመናል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች በህግ አግባብ የተደረገ የስጦታ ዉል አላቀረበም የሚል ከዉል ፎርም ጋር የተያያዘ ክርክር አቅርበዋል፡፡ እንደሚታወቀዉ ዉል አንድ የተወሰነ ፎርም ተከትሎ እንዲደረግ በህግ በልዩ ሁኔታ የተደነገገ እንደሆነ ዉሉ ህጋዊ ዉጤት ያስከትል ዘንድ በህግ የተወሰነዉን ፎርም ተከትሎ ሊደረግ ይገባል፡፡ የዉል ፎርም እንደየዉሉ እና የተጠየቀዉ ፎርም ዓይነት የተለያዩ ዓላማዎቹ ያሉት ሲሆን ከዚህ ዉስጥ አንዱ ዉሉ መደረጉን በተመለከተ ክርክር ሲኖር በማስረጃነት እንዲያገለግል ነዉ፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በስጦታ ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል በጽሑፍ ሆኖ ቢያንስ በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ እንዳለበት የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2443 እና 881(1) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የከተማ ይዞታን በስጦታ ለማስተላለፍ የሚደረግ የስጦታ ዉል የሚደረግበትን ፎርም አስመልክቶ በልዩ ሁኔታ የተመለከተ ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ ከላይ በተመለከተዉ መልኩ በፍትሐብሔር ህጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለተያዘዉ ጉዳይም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች በይዞታዉ ላይ መብት አግኝቻለሁ ላሉት ምንጩ ስጦታ መሆኑን በክሱ ከገለጸ በእርግጥም ይዞታዉን በስጦታ ያገኘ ስለመሆኑ በህግ አግባብ የተደረገ ዉል አቅርቦ የማስረዳት ግዴታ ያለበት በመሆኑ ተጠሪዎች ከዉሉ ህጋዊነት ወይም ተገቢዉን ፎርም አሟልቶ የተደረገ ዉል በአመልካች አልቀረበም በሚል ያነሱት ክርክር በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 248 መሠረት ከግምት ዉስጥ ገብቶ በጭብጥነት ተይዞ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ነዉ፡፡ ክርክሩ መፋለምን የሚመለከት ወይም የዉል ይፈጸምልኝ ዳኝነትን የሚመለከት አለመሆኑ እንዲሁም ክሱ የቀረበዉ የስጦታ ዉሉ ተዋዋይ ባልሆነ ሦስተኛ ወገን ላይ መሆኑ ይህ ነጥብ በጭብጥነት እንዳይያዝ ምክንያት ሊሆን አይገባም፡፡

ስለሆነም የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የክርክር ነጥብ መሠረት ባደረገ መልኩ አመልካች በህግ አግባብ የተደረገ የስጦታ ዉል ያቀረበ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ እና በመመርመር አመልካች በክሱ መሠረት ተገቢ የሆነ ማስረጃ አለማቅረቡን በማረጋገጥ ክሱን ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ ትክክለኛ የክርክር አመራር እና የጭብጥ

አመሠራረት ሥርዓትን የተከተለ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ይህ በመሆኑም በስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናዉ ዉሳኔ በዚህ ችሎትም ሊጸና ይገባል የሚል ሃሳብ ስላለኝ ከሌሎች ባልደረቦቼ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኞ ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም